# ኢትዮጵያውያን ለምን ኦባማን ሊመርጡ ይገባል?

በዚህ አመት የሚደረገው የአሜሪካ ፕሬዜዳንታዊ ምርጫ በምንም መለኪያ ታሪካዊ እንደሆነ ሁሉም ሰው ይስማማል፡፡ አሜሪካ እንደ አገር በቡሽ አስተዳደር ስር መሰረታዊ ማንነቱዋ እንደተሸረሸረባት፣ በአለም ሕዝብ ዘንድ አሜሪካ የነበራት ክብርና አድናቆት በእጅጉ እንደቀነሰባት፣ የሚወደሰው ኢኮኖሚዋ እንደተናጋባት፣ ይህ ታሪካዊ ምርጫ ደግሞ ይህን ክፉ የስምንት አመት ጠባሳ ለማከም፣ አገሪቱ ወደቀድሞ ክብርዋ እንድትመለስ ለማድረግ፣ ሁሉም ዜጋ የአሜሪካዊነት እጣ ፈንታዬ ነው ብሎ የሚመካበትን ከትውልድ ትውልድ በሁሉም መልኩ የተሻለ ሕይወት የመጠበቅ ሕልሙን ከወደቀበት ለማንሳት ነው፡፡ አሜሪካ አዲሱን ምእተ አመትና በጣም እየተቀየረ ያለውን አለማችንን ባረጀ የመከፋፈልና የጡንቻ ፖለቲካ ትወጣዋለች ወይንስ በብልህነትና በታወቀችበት የበጎ ነገር ተምሳሌትነት አለሙን ትመራዋለች? የሚለው መሰረታዊ አቅጣጫ የሚወሰንበት ነው ይህ ታሪካዊ ምርጫ፡፡ እንደጊዜው ብቸኛ ልዕለ ሀያል አገር ደግሞ ይህ የአቅጣጫ ውሳኔ የሚመለከተው አሜሪካንን ብቻ ሳይሆን በተለያየ ደረጃ ይሁን እንጂ ሁሉንም የአለማችንን ክፍል መሆኑን ከማንም በላይ እኛ ኢትዮጵያውያን እንረዳዋለን፡፡ እኛ በአሜሪካን አገር የምንኖር ኢትዮጵያውያን ይህንን ታሪካዊ ምርጫ በአካል በመገኘት ለመመልከት በመቻላችን እድለኞች ነን፡፡ የአሜሪካ ዜግነት የተቀበሉት ኢትዮጵያውያን ወገኖች በዚህ ምርጫ እንደ ዜጎች በመሳተፍ የምርጫውን ውጤት በትንሹም ቢሆን ለመወሰን በመቻላቸው የሚያስቀና ብቻ ሳይሆን ይህ እድል የሌላቸውንም ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ወክለው ነውና የሚሳተፉት ይህ ሂደት በምንም አይነት በቸልተኝነት የሚያልፉት እንዳልሆነ አይዘነጉትም ብለን እናምናለን፡፡ በሂደቱ ለመሳተፍ ደግሞ በመጀመሪያ መመዝገብ ያስፈልጋልና በአሁኑ ወቅት የአሜሪካ ዜግነት ያላችሁ ግን ለመምረጥ ያልተመዘገባችሁ ወገኖቻችን ካላችሁ የመመዝገቢያው ጊዜ ከማለፉ በፊት በአስቸኩዋይ እንድትመዘገቡ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርብላችኹዋለን፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ እኛ ኢትዮጵያውያን እራሳችንን እንደ አንድ የመራጭ ሀይል ብንመለከተው መሰረታዊ ጥቅማችንን ለማስጠበቅ የምንችለው ማንን ብንመርጥ ነው? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ይህን ጥያቄ ደግሞ መመለስ የሚገባን በዚህ አገር እንደሚኖር፣ እነኝህ ተመራጮች በሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫ በቀጥታ እንደሚጠቀም ወይንም እንደሚጎዳ አካል በአንድ በኩልና ከትውልድ አገራችን ጋር የሚያያይዘን ክር እንዳልተበጠሰብን የመጀመሪያ ትውልድ ስደተኞች በሌላ በኩል ነው፡፡ የዚህ አገር ኑሮአችንን ለአብዛኛዎቻችን የተሻለ የሚያደርግልንን፣የምንወዳት የትውልድ አገራችንን አበሳ የሚያሳጥርልንን ነው መምረጥ ያለብን፡፡ በእኛ እምነት ለአብዛኛው በአሜሪካን አገር ለሚኖር ኢትዮጵያዊ (የአሜሪካን አገር ዜግነቱን ለወሰደም ሆነ ላልወሰደ፣ ሕጋዊ የመኖሪያ ፍቃድ ላለውም ሆነ ለማግኘት ለሚጣጣረው) ጥቅሙን ለማስጠበቅም ሆነ በትውልድ አገራችን የገጠመንን የግፍ አገዛዝ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመቀየር የሚደረገውን የዜጎቻችንን ትግል ለማገዝ በዚህ ታሪካዊ ምርጫ ባራክ ኦባማን ቢያንስ በሚከተሉት አምስት ምክንያቶች ያለምንም ማወላወል በገፍ ወጥተን መምረጥ አለብን እንላለን፡፡

1. በኢኮኖሚ ፖሊሲ ዙሪያ ባራክ ኦባማ የሚከተለው አቅጣጫ ይጠቅመናል፡፡ የባራክ ኦባማ የታክስ ፕላን በአመት ከ 200፣000 ዶላር በታች ለሚያገኘው ቅነሳ የሚያደርግ መሆኑ ቢያንስ ከ99 በመቶ በላይ ለሆንን ኢትዮጵያውያን ተጨማሪ ገንዘብ ኪሳችን ውስጥ የሚያስገባልን ነው፡፡ ፖሊሲው ስራ ለመፍጠር የሚያደርገው ጥረት ለብዙዎቻችን የተሻለ የስራ እድል ሊያስገኝልን የሚችል ነው፡፡
2. ብዙ ኢትዮጵያውያን ካለንበት የስራ ዘርፍ የተነሳ አስተማማኝ የሆነ የጤና ዋስትና የለንም፡፡ በዚህም ምክንያት ትንሽ ህመም ወይንም ያልታሰበ አደጋ በገጠመን ጊዜ ጥሩ ህክምና ለማግኘትም ሆነ ላገኘነው ህክምና ለመክፈል ከፍተኛ ችግር ውስጥ እንወድቃለን፡፡ የልጆቻችንን ጤንነት ለመንከባከብ የሚገጥመንን ችግር ሁላችንም በየቤታችን የምናውቀው ነው፡፡ የባራክ ኦባማ የጤና ፖሊሲ ሁሉንም በአሜሪካ የሚኖር ህዝብ የጤና ዋስትና ተጠቃሚ ስለሚያደርግ ብዙዎቻችን የዚህ ፖሊሲ ተጠቃሚዎች መሆናችን አያጠራጥርም፡፡
3. የብዙ ኢትዮጵያውያን የስኬት መለኪያ የራሳችን በተለይም የልጆቻችን ትምህርት መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በየጊዜው እያሻቀበ የመጣው የኮሌጅ ትምህርት ዋጋ ይህንን የራስ ማሻሻያ እድል

ለብዙዎቻችን እየዘጋብን ነው፡፡ ይበልጥ የሚያስፈራው ደግሞ ችሎታው እያላቸው ልጆቻችን ለስኬታቸው መሰረት የሆነውን ጥሩ የኮሌጅ ትምህርት በእኛ አቅም ማነስ ምክንያት እያጡት ነው፡፡ የባራክ ኦባማ የትምህርት ፖሊሲ ልጆቻችን በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ጥሩ ትምህርት እንዲያገኙ ብቻ ሳይሆን በወላጆቻቸው አቅም ማጣት ምክንያት ከኮሌጅ ትምህርት እንዳይስተጉዋጎሉ ያደርጋል፡፡ በዚህ ፖሊሲም በአሁኑ ጊዜ ኮሌጅ ለመግባት የሚፍጨረጨሩ ወጣት ኢትዮጵያውያንም ሆኑ ልጆቻችን በጣም ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

4. እንደሚታወቀው በዚህ አገር ያለን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ዘላቂ የመኖሪያ ፈቃድ የለንም፡፡ በፈቃድ አለመኖር ወይንም ፈቃድ በመጠበቅ የሚጉላሉ ብዙ ወገኖቻችን እንዳሉ ይታወቃል፡፡ የባራክ ኦባማ የኢሚግሬሽን ፖሊሲ እነኝህ ወገኖቻችን በተቀላጠፈ መንገድ የመኖሪያና የስራ ፈቃድ የሚያገኙበትን መንገድ ስለሚያመቻች በዚህ ፖሊሲ ብዙ ወገኖቻችን ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ በመጨረሻም
5. የምንወዳት አገራችን ሕዝብ በነፃነት ማጣት በነመለስ አምባገነንነት ስር በሚማቅቅበት በአሁኑ ወቅት፤ ሕብረተሰባችን የራሱን መሪዎች መርጦ፤ መብቱ ተጠብቆና ሰርቶ እንዳይበላ እግር ተወርች አስሮ የሚያሰቃየው መንግስት በቡሽ አስተዳደር ድጋፍና ችሮታ  እንደሆነ የሚኖረው ሁላችንም የምናውቀው ነው፡፡ ምንም እንኩዋን በአገራችን ያለው የነፃነት ትግል የሚወሰነው በህዝባችን ትግልና እኛም በውጭ በምንኖረው ወገኖቹ ድጋፍ ቢሆንም፤ የአሜሪካን አይነት ሀያል መንግስት የሚከተለው የውጭ ፖሊሲ ምን ያህል ጫና እንደሚፈጥር የምናውቀው ነው፡፡ ባራክ ኦባማ በተለያዩ ክፍለ አለማት በተለይም በአፍሪካ የሚገኙ አምባገነን መንግስቶችን "በፀረ-ሽብር ትግል" ስም መደገፍ በመርህና በሞራል እሳቤ ትክክል አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን በሱ አስተዳደር ጊዜ የህዝቦችን የነፃነትና የዴሞክራሲ ትግል እንደሚደግፍ ግልፅ አድርጎታል፡፡ ለዚህም ነው በአገራችን የሚኖረው ህዝብ ለባራክ ኦባማ ከፍተኛ ድጋፍ የሚያሳየው ብቻ ሳይሆን የሱን መመረጥ በከፍተኛ ተስፋ የሚጠባበቀው፡፡ እኛም በአገር ቤት ለሚሰቃየው ወገናችን ስንል ባራክ ኦባማን ለማስመረጥ መሞከር ግዴታችን የሚሆነው፡፡

ስለዚህ ለራሳችን ህይወት መሻሻል፤ ለልጆቻችን የወደፊት እድል እንዲሁም ለምንወዳት የትውልድ አገራችን ስንል ይህ ምርጫ የሰጠንን እድል ተጠቅመን ባራክ ኦባማን ለማስመረጥ ከልባችን መስራት ይጠበቅብናል፡፡ በየቤታችን ሆነን ማውራትና ከንፈር መምጠጥ የትም እንደማያደርስ ቢያንስ ከዚህ አገር ኑሮአችን የምንገነዘበው ነው፡፡ ስለዚህ የሚቀጥሉትን ሁለት ወራት ለምንወዳቸው ሁለት አገሮች ስንል ጊዜያችንንም ሆነ ገንዘባችንን ሰውተን ባራክ ኦባማን ለማስመረጥ እንነሳ፡፡ "ኢትዮጵያውያን ለኦባማ" በሚል በጊዜያዊነት የተቋቋቋመው ስብስብ ይህንን ጥረት ለማስተባበር በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ከልባችን እንተባበር፡፡
በመረጡት መሪ ለመተዳደር ሲሉ በአገራችን ለተሰዉትና በእስር ለሚሰቃዩት ወገኖቻችን ክብር የሚሰማን መሆኑን እኛ ያለምንም አደጋ ለመምረጥ ያገኘነውን እድል በመጠቀም እናሳይ!!

ኢትዮጵያውያን ለኦባማ፡፡
አድራሻ…